በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጉምሩክ ኮሚሽን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION

ቀን ኅዳር 26 2012
Date
ቁጥር 6.1/01S3/12
Ref.No.

ለጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ
ባሉበት

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በቁጥር ውምክሪአዳ/01/2969/19 ጥቅምት 24 ቀን 2012 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ የአ.አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የጻፈውን ደብዳቤ መነሻ በማድረግ በLC፣ CAD እና በTT ክፍያ ስርአት ወደ አገር ውስጥ እዲገቡ የውጭ ምንዛሪ ክፍያ ከተፈፀመባቸው ፈቃዶች መካከል በክፍልፋይ ጭነት ከፊሉ አገር ውስጥ ገብቶ በተለያየ ምክንያት አስመጪዎች ቀሪውን ወደ አገር ዉስጥ ማስገባት በማይፈልጉበት ወቅት ሙሉውን ታሳቢ በማድረግ ከከፈሉት ቀረጥና ታክስ ላይ ቀሪው እንዲመለስላቸውና የተበተነ ዲ/ዮን እዲሰጣቸው እንደሚጠይቁና የከፈሉትን ቀረጥና ታክስ ለመመለስ ጉምሩክ ወደ አገር ውስጥ ሳይገባ ለቀሪው ዕቃ ተመጣጣኝ የውጭ ምንዛሪ ተመላሽ መሆኑን ማረጋገጫ ከባንክ እዲያመጡ በሚጠይቁበት ጊዜ ባንኮች ጉምሩክ ለውጭ ምንዛሪ መመለስ በተመለከተ አይመለከተውም በማለት ምላሽ ለደንበኞቻቸው እንደሚሰጡና በዚህም ምክንያት ቁጥጥር ለማድረግ ችግር መኖሩን በመግለጽ የተከፈለውን የውጭ ምንዛሪ ያለጉምሩክ ጣልቃ ገብነት ባንኮች የሚቆጣጠሩበት መንገድ መኖሩን እና ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ በጉምሩክ በኩል ሊደረግ የሚገባው የቁጥጥር ሂደት ምን ሊሆን እንደሚገባ ማብራሪያ እንዲሰጥ መጠየቁን በማስታወስ የጉምሩክ ሚና ምን መሆን እንዳለበት በአባሪው ላይ በተገፀው መሰረት አሳዉቆናል፡፡

ስለሆነም የክፍልፋይ ጭነትን በተመለከተ ባንኩ የሰጠውን ማብራሪያ መነሻ በማድረግ እንዲከናወን እያሳወቅን የተላከውን ማብራሪያ 2 ገጽ አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ነሞምሳ መርጎ
የዕቃ አወጣጥ አሰራርና ድጋፍ
ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር(ተወካይ)

ግልባጭ፡-
- ለኮሚሽን ጽ/ቤት (ያለ አባሪ)
- ለኦፕሬሽን ዘርፍ (ያለ አባሪ)
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ (ያለ አባሪ)
- የዕቃ አወጣጥ አሠራርና ድጋፍ ቡድን
  ጉምሩክ ኮሚሽን

ለዘመናዊና ፍትሀዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን!!

☎ +251 116 62 98 00
Fax +251 116 62 98 19
✉ 2559
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa,Ethiopia

የሚያረጋግጥ ተጨማሪ ዲክላራሲዮን እንዲያቀርቡ ወይም እቃው የማይገባ ከሆነ የውጭ ምንዛሬው ተመላሽ የተደረገበትን ደረሰኝ እንዲያቀርቡ ተደገርጎ ግዴታቸው የሚወራረድ ሲሆን ይህን ካልተወጡ ግን በተመሳሳይ ዶሊኩሜንት ላይ በማስገባት ተጨማሪ የውጭ ምንዛሬ እንዳያገኙ እንደምናደርግና በዚህም የውጭ ምንዛሬን እንደምንቆጣጠር ይታወቃል ፡፡

ከውጭ ምንዛሬ ጋር በተያያዘ የጉምሩክ የቁጥጥር ሂደት ምን መሆን እንዳለበት በግልፅ በመመሪያችን ላይ የተቀመጠ ነገር ባይኖርም በመመሪያ ቁጥር FXD/07/1998 አንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ 9.2 ላይ የአስመጪዎችን የውጭ ምንዛሬ ግዴታ ባንካችን ማወራረድ እንዲችል ጉምሩክ ዋናውን ዲክላራሲዮን እና ኮመርሽያል ኢንቮይስ መላክ እንዳለበት ይደነግጋል ፡፡

ክፍልፋይ ጭነት ሆኖ ወደ ሀገር ውስጥ ሙሉ ለሙሉ እቃው ካልገባ የተከፈለውን የገቢ እቃ ግብር ለመመለስ አስመጪዎች የውጭ ምንዛሬ ገቢ ያደረጉበትን ደረሰኝ ከባንክ ይዘው እንዲመጡ የሚያደርገው የጉምሩክ የውስጥ አሰራር ዕቃው ወደፊት የማይገባ ከሆነ የውጭ ምንዛሬው መመለሱን ከማረጋገጥ አኳያ አጋዥ ስለሚሆን በባንኩ በኩል የሚደገፍ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

የኒህሳብ ታደሰ
ዳይሬክተር የውጭ ምንዛሬ ክትትልና
ሪዘርቭ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

ግልባጭ

- ለምክትል ገዥ እና ቺፍ ኢኮኖሚስት /ሞኒተሪ ስታብሊቲ/
  ኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
  <u>አዲስ አበባ</u>